# የሸንጎ ድምፅ

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

Telephone +44 7937600756 , +1 9168486790

## የምስራች የሸንጎው ድምጽ ተበሰረች

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ የተራራቀውን የምታቀራርብ፣የተለያየውን የምታገናኝ፣ የተለያዩ አመለካከት ያላቸው ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩና የማያውቁትን ለማሳወቅ፡ የሚያውቁትን ደግሞ ለማካፈል እንደዚሁም በአገራችን ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ርዕሶችን እያነሳች ለአንባቢ በማቅረብ የተሻለ መግባባትና ግንዛቤ እንዲፈጠር ለማድረግ “የሸንጎ ድምጽ”የተሰኘች ልሳኑን ሲያቀርብ በሙሉ ደስታ ነው። የሸንጎው ድምጽ የሸንጎውን እድገትና እርምጃ፣የአገራችንን የታሪክ፣ የባሕል፣የኤኮኖሚና የፖለቲካ ርዕሶች ዙሪያ የምሁራንን የጥናት ውጤት ዘገባዎችን ታቀርባለች፣ ስነጽሁፍ፣ከአንባቢ የሚቀርቡ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን ይዳስሳሉ።በተጨማሪም “አገር እንዴት ሰነበተች?” በሚለው አምድ የአገራችንን ሁኔታ በመከታተል ለእንባቢያን ለማሳወቅ ጥረት ይደረጋል።

ለዚህ ሁሉ መስተንግዶ የሸንጎው አባላትና ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆኑ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ተሳትፎ አስፈላጊና ወሳኝ ነው።ገንቢ የሆኑ የተለያዩ አስተያየቶችን እናስተናግዳለን።የነጻ አምድን ምንነትና ጥቅም በተግባር የምንተረጉምበት ዕድልና መንገድ ይሆናል ብለን እንገምታለን።ለመሻሻል፣ ለእድገትና፣ለለውጥ የሚረዱ ሃሳቦችን በጽሁፍ ለሸንጎ ድምጽ በመላክ የዜግነት ድርሻዎን ይወጡ። እውቀትዎን ያካፍሉ፣ለሰላምና ለአንድነት ወጣ ብለው ሃሳብዎን በብዕር አንደበት ለማሰማት ቢነሱ የሸንጎው ድምጽ የእርሰዎም ድምጽ ሆኖ ያስተጋባልዎታል።በተጨማሪም የሸንጎውን ወይብ መጎብኘት ይቻላል፤

ሸንጎው በግንቦት ወር ከተመሰረተ በኋላ ላለፉት ስድስት ወራት የተመሰረተበትን ዓላማና ራሱን ከሕዝብ ጋር ለማስተዋወቅ ከፍተኛ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። የሸንጎው

## የሸንጎው የሥራ አስፈፃሚ መልእክት

አመራር አባላት የተለያዩ የኢትዮጵያ የሚዲያ አውታሮችን፤ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ድህረ ገፆችን በመጠቀም የሸንጎው ራዕይና ግቦች እስመልክቶ እንዲሁም ለሃገራችንና ለሕዝባችን አንገብጋቢ የሆነውን የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚቻልበትን አማራጭ መንገድ ለማሳየት ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል።

የሸንጎው ምክር ቤት ተደጋጋሚ ስብሰባዎችን በማካሄድ የሸንጎውን መዋቅርና አደረጃጀት ለማጠናከርና ሥራዎቹን ለማከናወን እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራዊ ኮሚቴዎችን አቋቁሟል፤ የሚገለገሉባቸው ሕገ ደንቦችንና የውስጥ መመሪያዎችን ቀርጿል።

ከሕብረተሰባችን ጋር በቅርበት ለመወያየት በማቀድ በሰኔ ወር ታላቅ ህዝባዊ ስብሰባ በዋሺንግተን ዲሲ ሲያካሂድ በነሐሴ ወር ደግሞ በቶሮንቶ ካናዳ ተመሳሳይ የሆነ ሸንጎው በአንድ በኩል ራሱን ለመጠናከር ሲሰራ፤ በሌላ በኩል ሌሎችን ለማሰባሰብና አብሮ ለመስራት የተለያዩ የዴሞክራሲ ኃይሎችን በመቅረብ ሠፋ ያለ በጋራ አብሮ የመሥራት እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ከፍጠኛ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በዲፕሎማሲው መስክም ሸንጎው መመሪያ ነድፎና ዕቅድ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ከአሜሪካ መንግስት ተቋማትና የሕዝብ ተወካዮች ጋር ግንኙነቶችን በፊት ለፊትና በተለያዩ መንገዶች በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብና የአገሪቱ ዘላቂ ጥቅም የሚከበረው

የሸንጎ ድምፅ

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

Telephone +44 7937600756 , +1 9168486790

መሠረታዊ የሆኑ የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ሲከበሩና ከአምባገነኖች ሲላቀቅ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲያስገነዝብ ቆይቷል።

ወደፊትም ከሌሎቹ የዴሞክራሲ ሀይሎች ጋር በመሆን በጋራ በመሰረቷቸው የተለያዩ ግብረ ሀይሎች ተመሳሳይ የውጭ ጉዳይ፣ የአቅም ግንባታ፣ የሕዝባዊ እንቅስቃሴና አውደ ጥናቶችን ለማካሄድ እያቀደና እየሰራ ይገኛል።

ሆኖም ግን ኢትዮጵያዊያን ሙሉ ለሙሉ መተማመን ያለባቸው በራሳቸው ላይና ለውጥ ለማምጣት ባላቸው ፍላጎት  የተግባር ሥራ ላይ በብቃት ተዘጋጅተው ሲሳተፉ  ብቻ ነው። ይህ በቂ ዝግጅት በመጀመሪያ በቅጡ መደራጀትንና ተበታትኖና ተለያይቶ እየዋዠቀ የሚገኘውን ሠፊውን የተቃዋሚ ሃይል አሰባስቦ ሊታይ የሚችል የትግል አማራጭ ሆኖ መቅረብን ይጠይቃል።

በቅርቡ በአቶ መለስ ከሥልጣን መወገድ የተፈጠረው ያልተጠበቀ ሁኔታ የተቃዋሚ ሀይሉ ካወቀበትና በአንድ ላይ በመሰባሰብ  ሁኔታዎችን በአግባቡ ሊይዝ ከቻለ፣ እንዲሁም ከስሜታዊነት፤ ጀብደኝነት፤ ግትርነት፤ ተጠላላፊነት፤ ቡድናዊነት የፀዳና የሰከነ የወቅታዊ ሁኔታ ትንታኔዎች ማድረግ ከቻለ፣ እንደአግባቡም የትግል ስልቱን ከነደፈ፣ በአቶ መለስ እግር ሊቀጥል የሚፈልገው፤  አምባገነኑ ሥርዓት እየተዳከመ ሄዶ፤ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተሻለ ሁኔታ መፍጠር፤ ለሕዝብ የስልጣን የበላይነት በር ለመክፈት ይቻላል።

ሸንጎው ከዚህ አንፃር ከመጀመሪያው ጀምሮ ራዕዩን ግቡንና አላማዎቹን አንጥሮ አውጥቶ ያስቀመጠ ሲሆን አሁን ከተፈጠረውም ሁኔታ አንፃር መከተል ያለበትን አቅጣጫ ከነዚሁ እምነቶች አንፃር ነው የሚያየው።

በሸንጎው ዕምነት ለሥርዓት ለውጥ የምናደርገው የመጀመሪያው መሠረታዊ እርምጃ አንጥረን ባወጣናቸው የጋራ ራዕይና ዓላማዎች ዙሪያ በውጭ የሚገኘውን የተከፋፈለና የተዳከመ ሠፊውን የተቃዋሚ ጎራ አንድ ላይ በማሳለፍ፤ በሚሰጠው የጋራ ስትራቴጂ ዕቅድ በመመራት በውጭ በስደት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን በሺዎች በማቆም በሚፈጠረው የትግል ኃይል፤ ወሳኝ ለሆነው በአገር ውስጥ እንዲፈጠር ለሚፈለገው የሕዝባዊ እምቢተኝነት የትግል ማዕበል በተለያየ መልክ ይህ ነው የማይባል አስተዋፅዖ ማድረግ ነው።

የኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ የመላው ሕዝቧ እኩልነት በአስተማማኝ ሁኔታ ዘላቂነቱ የሚረጋገጠው ዴሞክራሲያዊ ስርአት እውን ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ ግብ ለመድረስ ተደራጅቶም ሆነ ሳይደራጅ የሚገኘው ሠፊው የተቃዋሚው ሃይል መተባበር ብቻ ሳይሆን፤ በተግባር መለስተኛ ልዩነቶችን ወደ ጎን ትቶ በዋና ዋና አላማዎች ዙሪያ በአንድነት  የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት በአፋጣኝ መንቀሳቀስ አለበት። ይህ ሳይሆን ቀርቶ በተልካሻ ምክንያቶች እያንዳንዱ ጉዳዩ የሚመለከተው ቡድንም ሆነ ዜጋ ይህንን ለማድረግ ተስኖት የአምባገነኖችን ዕድሜ እንዲራዘም ከፈቀደ፣ ወደፊት ሥርዓቱ እየወሰደን ላለው ለህልውናችን አስጊ ለሆነው ከፍተኛ አደጋና ቀውስ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ላለመከላከል ከወሰኑት እንደምንቆጠር መገንዘብ አለብን።

ሸንጎው የቀረፃቸው አንኳር መርሆዎችና ዓላማዎች አብዛኛውን ተቃዋሚ ሊያሰባስብ ይችላል ብሎ ያምናል፤ ከዚያም በኋላ ከተቀሩትም ጋር ለመሰባሰብ ባደረገው ጥረት በተወሰነ ደረጃ በነዚህ ዓላማዎች ዙሪያ አብዛኞቹ ልዩነት እንደሌላቸው ለመገንዘብ ችሏል። ነገር ግን አንዳንዶቹ ወሳኝ ባልሆኑ የአሠራርና የአካሄድ አስተሳሰቦች ልዩነት ብቻ

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

Telephone +44 7937600756 , +1 9168486790

አብረው ለመቆም እንደተሳናቸው በቀላሉ ሊታይ የሚችል ሆኗል። ስለዚህ ሸንጎው በአንድ በኩል የቀረፀውን ራዕይና ዓላማዎች ለሕዝብ ለማስተዋወቅና በዙሪያውም እንዲሰባሰቡና እንዲደግፉ በተቀዳሚነት እየሰራ ሲገኝ በሌላ በኩል ደግሞ ከሸንጎው ጋር መሠረታዊ ልዩነት ከሌላቸው ከጅምሩ አብረው ሊቆሙ ካልቻሉ ሃይሎች ጋር ከጋራ እንቅስቃሴም በላይ በጣም በተቀራረበና በተቀናጀ መልክ ለመታገል ጥረት ማድረጉን ይቀጥላል።

እዚህ ላይ በአንድ በኩል ሠፋ ያለውን በስደት የሚገኝ ሃይል የበለጠ ማሰባሰብ የሚቻልበትን መዋቅርና አደረጃጀት የመፍጠር አስፈላጊነትና ለዚያ የሚደረገው ጥረት እንዳለ ሆኖ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ሂደት ተጠናቆ ሁሉም ተጠቃሎ እስከሚመጣ በአሁኑ ጊዜ ባሉት የትብብር ትግሎች ዙሪያ ለመሰባሰብና ለመታገል እንደማይቻል እንደ ምክንያትነት ብቻ በመጠቀም በአጠቃላይ የሕብረተሰባችን በቅጡ ያለመደራጀት መሸፈኛ ሆኖ እንዳይቀርብ ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል። ይሄ ጉዳይ የተቃዋሚ ቡድኖች አመራር ድክመቶች ብቻ እንደሆነ በደፈናው መተው ያለበት ሳይሆን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሃላፊነት እንዳለበት በመቁጠር በአንድ ላይ ተፅዕኖ የማድረግና ተጠያቂነትም እንዲኖር ማድረግን ይጠይቃል። ከላይ የተጠቀሰውን ድረገጻችን በመጎብኘት ተጨማሪ መረጃና አገልግሎት ለማግኘት ይችላሉ።

## ሸንጎውና ዓላማው

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) ከሃያ ወራቶች በላይ የወሰደው የአንድነት ግንባር ምሥረታ ጉባኤ ዝግጅት ተጠናቆ ከስድስት ወራት በፊት ከሜይ 10-13 2012 ዓ.ም. ድረስ በካናዳ ዋና ከተማ ኦታዋ በተደረገው የልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣የሲቪክ ማህበራትና ግለሰቦች ጉባኤ የስምምነት ውጤት ነው።ለብዙ ዓመታት የጋራ ግንባር ምስረታ ጥረት የተደረገና ለአጭር ጊዜም ቢሆን ብቅ ብለው የጠፉ ሕብረቶች እንደነበሩ አይካድም።እነዚያ ብቅ ብለው የከሰሙ ግንባሮች እንዴትና ለምን እድሜአቸው እንዳጠረ መርምሮና አጥንቶ በተሻለ መልክ የተሳካ ግንባር መመሥረት ጊዜው ያስገደድ ነበር፣አሁንም ያስገድዳል። የግንባሩን አስፈላጊነት በማመንና ለስኬቱም የጋራ እምነትና ዓላማ መኖር ወሳኝ እንደሆነ በመቀበል ሁሉንም የሚያስማማ ራዕይ በመንደፍ ሸንጎ በሚል ስም ለመንቀሳቀስ በጉባኤው ተሳታፊዎች ሙሉ ድጋፍ ተወሰነ።

በዚህ እልህ አስጨራሽ በሆነው ጥረት ሁሉም እንዲሳተፍ አሉ ለተባሉት የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራትና ግለሰቦች ጥሪ ተደርጎላቸው ነበር። በሆነ ባልሆነ ምክንያትና ተመሳሳይ ጥሪ በማድረግ ለተደረገላቸው ጥሪ ጭራሹን መልስ ያልሰጡ ድርጅቶች ቢኖሩም ጥሪውን ተቀብለው ስድስት የፖለቲካ ድርጅቶች፣ አምስት የሲቪክ ማህበራትና አያሌ ታዋቂ ግለሰቦች የቦታ እርቀት ሳይገድባቸው ከአሜሪካ፣ከአውሮፓ በመምጣት የሸንጎው መስራችና አባል ሆነዋል። በተጨማሪም በታዛቢነት የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች እንደዚሁም ታዋቂ ግለሰቦች የተገኙ ሲሆን በጉባኤው ሂደት ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ በውጤቱም ደስተኞች ነበሩ፤ ከሸንጎውም ጋር አብሮ ለመሥራት ወይም ለመቀላቀል ፍላጎት እንዳላቸው በቦታው ገልጸዋል። ይህም ጉዳይ አሁን በተግባር በመተርጎም ላይ ነው።

ሁሉም የተሳሰሩበት ነገር ቢኖር የተስማሙበት ዓላማና ራዕይ ነው። ዘላቂ ራዕያቸው ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ሲሆን ለዚያ የሚያበቁ የዓላማ መርሆችን በግልፅ

አስቀምጦ መንቀሳቀስ ነው። እነዚህም ዋና መርሆዎች፣

፣1ኛ.በኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፣በሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና ልዑላዊነት ላይ ግልጽና የማያወላውል እምነት መያዝ፤

2ኛ.ፍትሕ የሰፈነባትና የሕግ የበላይነት የተረጋገጠባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ጸንቶ መታገል፤

3ኛ.በኢትዮጵያ ሕዝብ መካካል ምንም አይነት አድልኦ ሳይኖር ሁሉም ዜጋ በህግ ፊት እኩል መሆኑን ለማረጋገጥ መታገል፤

4ኛ.የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች መከበር እንዳለባቸው በማመን በድርጅቶች ውስጣዊ አሠራርም በተግባር እንዲተረጎም ጥረትና ትግል ማድረግ፤

5ኛ.የህወሃት/ኢሕአዴግ መንግሥትና ስርዓት የአፈናና የጭቆና ሥርዓት በመሆኑ መለወጥና በዲሞክራሲያዊ አስተደደር መተካት እንዳለበት በማመን ለዚያም መታገል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መርሆዎች ሁሉንም ለዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈን የሚሻውን ኢትዮጵያዊ የሚያስማሙና የሚሰበስቡ የጋራ ዓለማ መርሆዎች መሆናቸው አይካድም። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግለሰብም ይሁን ስብስብ፣የፖለቲካም ይሁን የሲቪክ ማህበር የጋራ ትግልን አስፈላጊነት ይዘነጋዋል ተብሎ አይታሰብም።በድርጅት የተካተቱም ይሁኑ ያልተካተቱ ለአገራቸው በጎ ነገር የሚሹና የሚመኙ ወሳኝ ለሆነው የአንድነት ግንባር ጥንካሬ ሸንጎው በጣለው መሠረት ላይ ቀሪ ግንባታ ውስጥ እንዲሳተፉ አሁንም ጥሪ ያደርጋል።ከአሁን በኋላ ለአንድነት ግንባር ጥንካሬ እያንዳንዳችን ለጥሪው የምንሰጠው መልስና ተሳትፎ ወሳኝ ነው። ግንባር የለም ብለን የምናመካኝበት ጉዳይ የለም። ያልጠነከረ ግንባር አለ በሸንጎው እርሾው ተጥሏል፤ ያንን ቀርቦ ማስፋትና ማጠናከር ለእውነተኛ ትግል፣ ለህብረት ሥራ የቆረጠ ወገን ድርሻ ነው።በድርጅት ላይ ድርጅት፣በግንባር ላይ ግንባር እያቋቋሙ እርስ በርስ የሚፋተጉበትና የሚዳከሙበት ጊዜ አይደለም፣ ሁሉም ወደ አንድ አቅጣጫ የሚሄድበት፣በአንድ እረድፍ ተሰልፎ የጋራ ጠላትን ተፋልሞ የሚጥሉበት ጊዜ ነው።

በአደጋ ላይ የሚገኘውን የአገር አንድነት አስከብሮ በእኩልነትና በዲሞክራሲ ስርዓት የሚኖሩበትን ዕድል ለመፍጠር የግዴታ ተሰባስቦ መነጋገርና ስልት መንደፍ፣ የተበታተነን ሃይል ማሰባሰብ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ለሚደረገው ጥረት የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) ያላሰለሰ ጥረት ይደርጋል። ከማንኛውም ዓላማውን ከሚቀበሉና ከሚጋሩት ጋር አብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ ነው።የሌሎችንም ሃሳብ ለመስማትና ዓላማውን እስካልተጻረረ ድረስ ለመቀበል ዝግጁ ነው። በዓላማ ልዩነት እንጂ በስልት ልዩነት ለመራቅና ለመለየት አይሻም። የአንድነት ግንባሩ እንዲሰፋና ብዙዎች የሚሳተፉበት የአገር አቀፍ ጉባኤ እንዲካሄድ ሸንጎው የሚያደርገውን ጥረት ይቀጥልበታል።

በተግባር የሚገለጽበት ጊዜ እሩቅ እንደማይሆንም ሙሉ ተስፋ አለው። ለስኬቱ የራቁት እንዲቀርቡ፣ ሁሉም ድርጅትና ግለሰብ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ያለመሰልቸት ጥሪ ያደርጋል።

ሸንጎው ከተመሠረተ በኋላ በተደረገው ጥረት የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት የሸንጎው አካል ሲሆኑ ሌሎችም እንዲሁ ለመቀላቀል

ውሳኔአቸውን ይፋ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ናቸው።

የውጩ ትግል ከውስጡ ትግል ጋር ካልተያያዘ ውጤት እንደማይኖር፣ቢኖርም ብዙ ውጣ ውረድ የሚበዛበት እንደሚሆን የታወቀ ነው። የውጩ ትግል ለውስጡ እረዳትና ደጀን እንጂ ተተኪና መሪ ሊሆን አይችልም። የውስጡ ትግልም ካለውጩ እርዳታና ተሳትፎ አቅሙ ደካማ ነው። የሁለቱ ትስስርና መተጋገዝ ለትግሉ የተሳካ ውጤት ዋስትና ነው። የውጩ በዲፕሎማሲና በአቅም ግንባታ በተለይም በገንዘብ፣ እንዲሁም በነጻ የመሰብሰብ ሃሳብን የመግለጽና የነጻ ሚዲያ ዘርፍ ለማቋቋም ችሎታና ብቃት ሙብትም ስላለው የተደበቁ ዜናዎችን እያወጣ፣ሕዝቡ የሚደርስበትን በደል እያጋለጠ ሕዝባዊ ትግሉ እንዲቀጣጠል ቅስቀሳ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ከውጭ አገር የሚተላለፉ የዜና አውታሮችን ማለትም የቪኦኤ፣ የጀርመን ራዲዮና የኢሳትን ስርጭት አገልግሎት እንዲሁም የተለያዩ ድህረገጾችን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል።

በአገር ውስጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ደግሞ ሕዝብን በማደራጀት፣በመቀስቀስና በመምራት ትልቅ ሚና መጫወት ይገባል። ሙብት በትግል እንጂ በፈቃድ የማያገኙት መሆኑን ተገንዝበው የሚጠበቅባቸውን በተግባርና በድፍረት ማሳየት ይኖርባቸዋል። ትግል ደግሞ መስዋእትነትን ይጠይቃል። ሙብት በተለይም የሥርዓት ለውጥ ለምነውና ተለማምጠው የሚያገኙት ስጦታ አይደለም።

የሥልጣኑ ጥያቄ በተባበረ ክንድ ህወሃት/ኢሕአዴግ ተወግዶ ከሚፈጠረው ከሽግግር ወቅት በኋላ የሚነሳጉዳይ ነው ብሎ ሸንጎው ያምናል።

## እንኳን ደስ አላችሁ

ሰላምታየ ይድረሳችሁ!
በቅርቡ ሸንጎው የራሱ የሆን መፅሄት ለማዘጋጀት እንዳቀደ ተረድቻለሁ። ይህ እርምጃ አበረታች እና ትክክለኛም ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ሕትመት ሸንጎውን ለአባላቱ፣ ለደጋፊዎች እና ለሌሎችም የኢትዮጵያን እና የህዝቧን ጥቅም የሚያንፀባርቅ ፅሁፍ ለማቅረብ እና ሃሳብ ለማካፈል ያስችለዋል።

ምሁራን ፣ ታዋቂ ፀሀፊዎች እና ሌሎችም ይህንን አዲስ መፅሄት(ህትመት) እንደራሳቸው በማየት ሃሳባቸውን ለህዝብ ለማጋራት እንደሚጠቀሙበት ተሰፋ አደርጋለሁ።

በእኔ በኩል ከሙያዬ ጋር የተያያዘ እና በሀገራችን ውሰጥ በሚታየው ንቅዘት ላይ ያተኮረ ፅሁፍ ጊዜ በፈቀደልኝ መጠን ለማበርከት እና ለአንባቢያን ለማቅረብ ፍላጎቴ ነው።

ከሰላምታ ጋር
ሰኢድ ሃሰን፣የ ኢኮኖሚከስ ፕሮፌሰር፣
መሪ ሰቴት ዩኒቨርሰቲ;
ኬንታኪ፣ አሜሪካ

## ማሳሰቢያ

በሚቀጥለው እትማችን በሸንጎው የትግል አቅጣጫ እና ሌሎችም ወቅታዊ ርእሶች ላይ ያተኮሩ ጽሁፎችን ይዘን እንቀርባለን;;
በዚህ የመጀመሪያ እትም ላይ ወይንም በማንኛውም ሸንጎውን የተመለከት ጉዳይ ላይ አሰተያየት ለመሰጠት ቢፈልጉ በሚከተለው አድራሻወቻችን ሊያገኙን ይችላሉ፡
የ ኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)
www.ethioshengo.org
shengo.derbiaber@gmail.com
ሰልክ +44 7937600756 ወይም +1 9168486790